DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በጸደይ 2019፣ የእርስዎ ልጅ አገር አቀፍ የሆነውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት/የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ (ELA) እና/ወይም ሂሳብ ምዘና ወስዷል።

በDC ለአምስተኛ ጊዜ በተርታ፣ የኛ አመታዊ ምዘናዎች ለተማሪዎቻችን በጣም አስፈላጊ የሆኑ እውቀት እና ክህሎቶችን -ክህሎቶች እንደ መጻፍ፣ ችግር መፍታት፣ እና ሌላ በሂሳብ እና ELA መተማመን እና ስኬትን የሚያመጡ መሰረታዊ ህክሎቶች ለክተዋል።

ልጅዎ ላጠናቀቀው እያንዳንዱ ምዘና ከልጅዎ ትምህርት ቤት የውጤት ሪፖርት ያገኛሉ። ይህ መምሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊማሩ የሚችሏቸውን አስፈላጊ ነጥቦችን ይመራዎታል እና ልጅዎ በቀጣይ አመት ለማሻሻል እንዲረዳው ግብአቶችን ያቀርብልዎታል። የልጅዎን የውጤት ሪፖርቶች ካልደረሱት፣ እባክዎ ቅጂውን ለመጠየቅ ልጅዎ በ2018-2019 የተማረበትን ትምህርት ቤት ያግኙ።

የምዘና ነጥቦች የልጅዎን ሙሉ የአካዳሚክ ታሪክ እንደማይናገር እኛ እናውቃለን። ውጤቶቹ ከብዙ መለኪያዎች ውስጥ አንዱ ነው- የሪፖርት ካርድ ውጤት፣ የክፍል አፈጻጸም፣ እና የአስተማሪ ግብረመልስን የሚያካትት- ሁሉም ባንድ ላይ ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን እድገት ምስል የሚፈጥሩ። በዚያ ምስል ውስጥ፣ አመታዊ ምዘናዎቹ እርስዎ እና የልጅዎ አስተማሪዎች የእርስዎ ልጅ ባለፈው አመት ለELA እና ሂሳብ የመንግስት የይዘት መስፈርቶች ልጅዎ ያሳየውን እድገት በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ የተሰሩ ናቸው።

ልጅዎ በELA እና የሂሳብ ምዘናዎች ላይ ያለው ነጥብ በደምብ እየሰሩ ያለበትን ወይም የበለጠ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ቦታ ለማሳየት ተከፋፍለዋል። በሚቀጥለው አመት፣ የልጅዎ አስተማሪዎች ተጨማሪ እርዳታ ለመስጠት ወይም የበለጠ ፈታኝ ስራ ሲያስፈልግ ይህን  መረጃ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ይህን መረጃ የመማሪያ ጊዜ በቤት ውስጥ ለማተኮር ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

በመጨረሻ፣የኛ ግብ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ማዘጋጀት እና ህልሞቻቸውን እና ፍላጎታቸውን እንዲያሳኩ ማድረግ ነው። አጠቃላይ ጥያቄዎች ካሎት ወይም ስለ ምዘናዎች የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ የኛን ድህረገጽ osse.dc.gov/parcc ላይ ይጎብኙ ወይም ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ይወያዩ ። በተጨማሪ በዚህ መምሪያ ገጽ 4 ላይ ያሉትን ግብአቶች መጠቀም ይችላሉ።

OSSE ውስጥ፣ ሁሉም ተማሪዎች ሊማሩ እና ከፍተኛ ደረጃ ሊደርሱ እንደሚችሉ እናውቃለን እና ልጅዎ እንዲሳካለት ከእርስዎ ጋር በአጋርነት የመስራት እድሉን እናደንቃለን።

እናመሰግናለን፣

ሃንሰውል ካንግ
የዲሲ እስቴት የትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ

# የውጤት ሪፖርትን ማከፋፈል፡ ፊት

ይህ መመሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊረዱ የሚገባዎትን በጣም አስፈላጊ ግንዛቤ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይመራዎታል። በመጪው ዓመት ልጅዎ አሰራሩን እንዴት እንደሚያሻሽል ጠቃሚ መረጃዎችን ይሠጥዎታል።



## ሒሳብ

ስኮት ቴስትቴከር
Anywhere Middle School

የ 7ተኛ ክፍል የምዘና ውጤቶች
DC Public Schools

### ስለዚህ ምዘና በተመለከተ

ስኮት የ PARCC (Partnership for Assessment of Readiness for College and Careers) ን የሒሳብ ፈተና በጸደይ 2019 ላይ ወስዷል። PARCC ...ሪዎች በጥልቅ እንዲያስቡ፣ ችግሮችን እንዲፈቱ፣ እና በዚህ የክፍል ደረጃ ...ኮርስ፣ እንዲሁም በስተመጨረሻ በኮሌጅ እና እና በሥራ ዓለም ላይ ...ማ ለመሆን የሚያስችላቸውን እውቀት እና ክህሎት የሚመዝኑ ጥያቄዎች ...ት እንደሚመልሱ ይጠይቃል። እነዚህ ውጤቶች የስኮትን ፍላጎት እና ...ሬ ለመረዳት ከሚያስችሉት ብዙ መንገዶች ውስጥ መካከል ናቸው። በዚህ ...ረጃ መሰረት፣ ቤተሰቦች ለልጆቻቸው ድጋፍ ለማቅረብ ግብአቶችን መለየት ላይ ከመምህራኖች ጋር እና ከትምህርት ቤቶች ጋር አብረው ሊሰሩ ይችላሉ። ትምህርት ቤቶች በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረበውን መረጃ በመጪው ዓመት ላይ ለተማሪዎች በተሻለ መልኩ የሚያስተምሩበትን ዘዴ እና ማበልጸጊያቸውን ለማቀድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ስለዚህ ሪፖርት ምንም ዓይነት ጥያቄዎች ያሎት እንደሆነ፣ እባክዎን የስኮትን አስተማሪ ወይም ዋና ሃላፊ ያነጋግሩ፣ ወይም DCPS በ (202) 442-5885ላይ ደውለው ያግኙ።

ስለ PARCC ፈተና ምንም ዓይነት ጥያቄዎች ያሎት እንደሆነ፣ OSSE ን በ (202) 719-6500ላይ ደውለው ያግኙ።

### ይሄንን ሪፖርት እንዴት ለመጠቀም ይችላሉ?

ይሄ ሪፖርት ስለ ስኮት ክህሎቶች መጎልበት ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያግዞታል፡

- ስኮት እንዴት ዓይነት ውጤት አገኘ?
- በዚህ ትምህርት ላይ የስኮት ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ምንድን ነው?
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር የስኮት ውጤት እንዴት ይመስላል?

### በዚህ የሒሳብ ምዘና ላይ ስኮት ምን ያህል ውጤት አገኘ?

ይሄ ክፍል በምዘናው ላይ ልጅዎ ያገኘውን ጠቅላላ ውጤት ያሳዮታል። ውጤቱ የእርስዎ ተማሪ በየትኛው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይወስናል።

የአፈፃፀም ደረጃ
ደረጃ 4

ውጤት
760

ደረጃ 4 ውጤት ያመጡ ተማሪዎች
ለ 7ተኛ ክፍል የመማር መስፈርቶች ላይ
የሚጠበቅባቸው ደረጃ ላይ ደርሷል።



- ደረጃ 1የሚጠበቅበትን እስካሁን አላሟላም
- ደረጃ 2 በከፊል የሚጠበቅበትን አሟልቷል
- ደረጃ 3 የሚጠበቅበት ላይ ደርሷል
- ደረጃ 4 የሚጠበቅበትን አሟልቷል*
- ደረጃ 5 ከሚጠበቅበት በላይ አሟልቷል*

*ደረጃ 4 እና 5 ለሚቀጥለው የክፍል ደረጃ እና ሃይ ስኩልም ለመልቀቅ እና ለኮሌጅ እና ለሥራ ዓለም ዝግጁ መሆን ያመላክታል

### የበለጠ ለማወቅ ይፈልጋሉ?

በምዘናው ቁልፍ ነገሮች ላይ እንዴት ስኮት እንደሰራ፣ የስኮት ውጤት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እንደሚነፃፀር ለማወቅ የሚቀጥለው ገጽ ላይ ይሂዱ።

## 1) የፈተናው መግለጫ

በሪፖርቱ ጫፍ ላይ አጭር የፈተናው መግለጫ አለ። ስለዚህ ሪፖርት ጥያቄዎች ካሉዎት በዚህ አንቀጽ መጨረሻ ላይ ያለውን አድራሻ ይመልከቱ።

## 2) በጠቅላላ የልጅዎ ውጤት እንዴት ነበር?

የልጅዎ ውጤት ከአምስቱ አንዱ የውጤት ደረጃዎች ውስጥ ይካተታል። የውጤት ደረጃዎቹ የልጅዎ ውጤት ምን ውስጥ እንደሚገባ እና ልጅዎ ለክፍል ደረጃው/ዋ የሚጠበቀውን አሟልቶ/ታ እንደሆነ ይጠቁማል። በደረጃ 4 ወይም 5 የሆነ ውጤት ልጅዎ በትምህርቱ የሚጠበቅበትን/ባትን ወይም ከሚጠበቀው በላይ አግኝቷል/ታለች ማለት ነው። በተጨማሪም ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁነት ትክክለኛውን አቅጣጫ ይዟል/ዛለች ማለት ነው። ከደረጃ 4 በታች ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች አሁንም የክፍል ደረጃ ችሎታዎች እና ዕውቀት ሊያዳብሩ ይችሉ ይሆናል።

# የውጤት ሪፖርትን ማከፋፈል፡ ጀርባ

## 3) ልጅዎ ልዩ እውቀትን እና ችሎታዎችን ምን ያህል ተምሯል?

ተማሪዎች ስለ ጥንካሬያቸው እና የቱ ጋር ተጨማሪ ደጋፍ ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል በበርካታ ክፍሎች የበለጠ ዝርዝር የሆነ መረጃ ያገኛሉ። ለእያንዳንዱ ክፍል የቁጥር ነጥብ ባይሰጥም፣ ሪፖርቱ በዚህ ክፍል ውስጥ ለተዘረዘሩ ለእያንዳንዱ ቁልፍ የግምገማው ክፍል ተማሪ ዎ የተጠበቀውን ወይም ከዚያ በላይ፣ የተጠበቀው አከባቢ ወይም ከተጠበቀው በታች ካመጡ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ አፈጻጸም ማድረግ አለማድረጉን ያሳያል።



3

7ተኛ ክፍል የሒሳብ ዝርዝሮች

የአፈፃፀም ደረጃ
ደረጃ 4

ስኮት የምዘናው ቁልፍ ክፍሎች ላይ ምን ዓይነት ውጤት አመጣ?

...ህ ምዘና ላይ በአጠቃላይ በደረጃ 4 ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የመማር ግምቶች አሳክተዋል እና ለሚቀጥለው ክፍል ወይም ኮርስ ዝግጁ ናቸው። ...ፍል ልጅዎ የሚጠበቅባቸውን ያሟሉ ወይም ያለፉ፣ የሚጠበቅባቸው ነገር ላይ የደረሱ፣ ወይም ያላሟሉ ወይም በከፊል የሚጠበቅባቸውን ያሟሉ ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር ምን ...ውጤት እንዳመጣ ያሳያል።

| ዋና ይዘት | ተጨማሪ እና ደጋፊ ይዘት | የሒሳብ ምክንያታዊነት አገላለጽ | ሞዴል ማድረግ እና አተገባበር |
|---|---|---|---|
| አሟልቷል ወይም አልፏል ✓ | ከታች — | ለማሟላት ተቃርቧል • | አሟልቷል ወይም አልፏል ✓ |
| ራዲካሎች/ኤክስፖነንቶች፣ ፋንክሽኖች፣ ፓይታጎራስ ቲዮረም | ምክንያታዊ ያልሆኑ ቁጥሮች፣ ይዘት፣ ስካተር ፕሎቶች | መፍትሔዎችን ማሳመን እና የሌሎችን ምክንያታዊነት ማረም | ምልክቶችን እና መገልገያዎችን በመጠቀም ችግሮችን ለይቶ መፍታት መቻል |

✓ የሚጠበቅበትን አሟልቷል ወይም አልፏል • የሚጠበቅበትን ለማሟላት ተቃርቧል — ከተጠበቀው በታች

የስኮት አፈፃጸም ከሌሎች ጋር ሲወዳደር ምን ይመስላል?

4



ከጥሎ የሚሆነው ምንድን ነው?

ይሄንን ሪፖርት ከተማሪዎ መምህር ጋር በሚደረገው ቀጣዩ ስብሰባ ላይ ያምጡት። የስኮትን መምህራኖች የሚከተሉትን መጠየቅ ይችላሉ፡

- በዚህ ዓመት ሒሳብ ውስጥ ስኮት ምን እንደሚማር?
- ስኮት እንዴት እየሰራ ነው?
- በዚህ ዓመት ከስኮት ጋር አብሬ ለመስራት እንዴት ይሄን መረጃ እጠቀማለሁ?
- ስኮትን ለመደገፍ የትኛዎቹን ግብአቶች መጠቀም እችላለሁ?

የበለጠ መረጃ የት ማግኘት እንደሚችሉ መጠየቅ?

- የስኮት ትምህርት ቤት እና ለሌሎች ትምህርት ቤት ምን ዓይነት ውጤት እንዳመጡ፡
ይጎብኙ Results.OSSE.DC.gov ወይም DCPS (202) 442-5885 ላይ ይደውሉ።
- ፈተናው እንዴት እንደተዘጋጀ እና ምን እንደሚመዝን፡
ይጎብኙ PARCConline.org ወይም OSSE (202) 719-6500 ላይ ይደውሉ
- እነዙህን ሪፖርቶች ቤተሰቦች፣ አስተማሪዎች፣ እና ትምህርት ቤቶች ይጠቀማሉ፡
ይጎብኙ OSSE.DC.gov/parcc ወይም OSSE (202) 719-6500 ላይ ይደውሉ

5

## 4) ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር እሱ/ሷ ውጤት እንዴት ነበር?

ይህ ሪፖርት የልጅዎ ውጤት በትምህርት ቤት ደረጃ፣ የሀገር ውስጥ የትምህርት ድርጅት ደረጃ፣ እና በዲስትሪክቱ ውስጥ ከእኩዮቹ ጋር ሲወዳደር ውጤቱ ምን ያህል እንደሰራ ያሳያል። በተጨማሪም፣ ያለፈው ዓመት የልጅዎ ውጤት በዲሲ አካባቢ ፈተናውን ከወሰዱ ተማሪዎች ጋር እንዴት እንደሚወዳደር ያሳያል።

## 5) የሚቀጥለው ምንድነው?

በውጤቱ ሪፖርት ላይ ያለው መረጃ የተማሪውን እድገት ለመለካት እና ችሎታን ለመገንባት መመምሪያ ለማስጠት የተዘጋጀ ነው። ይህ ክፍል የልጅዎን አስተማሪ ስለ አሰራሩ/ሯ ሊጠይቁ የሚችሉትን ጥቂት ጥያቄዎችን ያቀርባል። ተጨማሪ መረጃን የት እንደሚያገኙም ያካፍላል።

ግብዓቶች እና ድጋፍ

ልጅዎ ብቃቱን/ብቃቷን እንዲያሳድግ/እንድታሳድግ የሚያግዙ በርካታ ጠቃሚ ግብዓቶች እንዲሁም፣ የልጅዎትን የነጥብ ዘገባ በተመለከተ ከልጅዎት እና ከልጅዎት መምህር ጋር ለመወያየት ጠቃሚ የሆኑ ምክሮች ቀጥሎ ቀርበዋል፥

## ስለ ዲሲ የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ነጥቦች ወይም የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና የበለጠ ለማወቅ ይፈልጋሉ?

ስለ የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና እና የጋራ ዋና የእስቴት ደረጃዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ድህረ ገጾች ይጎብኙ፥

- OSSE.dc.gov/parccበነጥብ ዘገባዎቹ፣ የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና እና በየጋራ ዋና የእስቴት ደረጃዎች ዙሪያ ስለዲሲ ውስን መረጃዎች ከፈለጉ።
- Results.OSSE.dc.gov የልጅዎት ትምህርት ቤት እና ሌሎች በዲሲ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ያስገኙት ውጤት ምን እንደሚመስል መረጃ ለማግኘት።
- PARCConline.org ለወላጆች እና ለተማሪዎች ስለ ምዘናዎቹ እና ስለ ግብዓቶቹ መረጃ ለማግኘት።
- CoreStandards.org ስለ የጋራ ዋና የእስቴት ደረጃዎች የበለጠ ለማወቅ።

## አሁን የልጅዎትን የፈተና ውጤት አግኝተዋል፣ ቀጣዩ ነገር ምንድን ነው?

ልጅዎ በትምህርቱ/ቷ እንዲሻሻል/እንድትሻሻል ለማገዝ ይችሉ ዘንድ እነዚህን ግምገማዎች እንዲጠቀሙ የሚያግዙ በርካታ መርጃዎች አሉ፥

- GreatSchools.org የትምህርት ይዘት እና የክፍል ደረጃ ተኮር የሆኑ ቪዲዮዎችን የሚያቀርብ ሲሆን በቤት ውስጥ ከልጅዎት ጋር ትምህርት እና ልምምዶች ማካሄድ ይችላሉ።
- BeALearningHero.org በክፍል ደረጃ፣ በትምህርት ዓይነት እና በትምህርት ይዘት መሰረት ለዲሲ ግብዓቶችን የሚያበጁ ክህሎት ገንቢ ገጽን እና የትምህርት መሳሪያዎች ገጽን ጨምሮ ለወላጆች ብዙ ግብዓቶች አለው።
- PRC.PARCCOnline.org በተጨማሪም ከ 3ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመለማመጃ ፈተናዎች እና የናሙና ጥያቄዎች ያቀርባል።

## ከልጅዎ ጋር ስለ ውጤቱ/ቷ ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በመነጋገር ረገድ የተካኑ ናቸው። ቀጥሎ ስለ ልጅዎት የፈተና ውጤት በሚያወሩበት ጊዜ ማስታወስ ያለብዎት ጥቂት ጠቃሚ ነጥቦች ተዘርዝረዋል፥

- የፈተና ውጤቶች አንድ የአፈፃፀም ልኬት ብቻ ናቸው።
- በጠንካራ ጎኖቻቸው ላይ ትኩረት ያድርጉ።
- መሻሻል የሚሹ ዘርፎችን ተደራሽ ለማድረግ ስልቶችን ይወያዩ (ለምሳሌ፥ በቤት ውስጥ ሳይንሳዊ ሀሳቦችን መመርመር፣ ከአስተማሪ ጋር መስራት)።

## ከልጅዎ መምህር ጋር ስለ ልጅዎ ውጤት ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ከልጅዎ መምህር ጋር የሚደረግ ውይይትን ለመምራት የሚረዱ ጥቂት ጥያቄዎች ናቸው፥

- በዚህ ዓመት በሂሳብ የልጄ የትምህርት ግቦች ምንድን ናቸው? በንባብስ?
- ልጄ በሂሳብ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ እያሳየ/ች ያለው/ችው ብቃት ምን ይመስላል? በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርትስ?
- ልጄ እነዚህን ግቦች ለማሳካት በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ ምን አይነት ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልገዋል/ጋታል?
- በእርሶ ምልከታዎች መሠረት፣ ልጄ በጥሩ ሁኔታ እየሰራ/ች ያለው ምንድን ነው? ለልጄ ማሻሻል የሚያስፈልጋቸው ዘርፎችስ የትኞቹ ናቸው?